Attention to Kassahun Kidane

# የገቢዎች ሚኒስቴር

## መመሪያ ቁጥር 7/1996

### በልዩ መብት ከቀረጥና ታክስ ነፃ እና ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ የግል መገልገያ እቃዎች ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው ጓዛቸውን ጠቅልለው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን፣ የኢትዮጵያ ተወላጅ የውጭ ዜጎች የሚያስገቧቸው የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች አግባብ ካለው የመንግሥት መ/ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኙ የውጭ ባለሀብቶች እና በውጭ አገር በዘላቂነት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች እንዲሁም በኢትዮጵያ ለመኖር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ የውጭ ዜጎች/ሰዎች ለግል መገልገያ ስለሚያስገቧቸው ዕቃዎች አፈፃፀም ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ተሻሽሎ በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/1995 አንቀጽ 3 መሠረት የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ እንደሚያወጣ የተደነገገ በመሆኑ፤

የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብ ቁጥር 122/85ን ለማሻሻል በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 6/88 አንቀጽ 2 መሠረት የጉምሩክ የዕቃ ቀረጥ ሥርዓትና ተመን ሁለተኛ መደብ አንቀጽ ለ (2) ለ (እንደተሻሻለው) በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው ጓዛቸውን ጠቅለው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን እና በተራድኦ ስምምነት መሠረት የሚመጡ የውጭ ዜጎች ከቀረጥ ነፃ የሚያስገቧቸውን የግል መገልገያ ዕቃዎች ዝርዝር የፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ቦርድ እንደሚያወጣ የተደነገገ እና ይህም ለገቢዎች ሚኒስቴር የተላለፈ በመሆኑ፣

እስካሁን በሥራ ላይ ያለው መመሪያ በርካታ ጊዜያት ማሻሻያ የተደረገበት በመሆኑ ለአጠቃቀም አመቺ ካለመሆኑም በላይ በአፈፃፀም ወቅት ለተከሰቱ በርካታ ችግሮች ለወደፊት መፍትሄ ለመስጠት እና ከዘመኑ የቴክኖሎጂና የአኗኗር ዕድገት አንፃር ነባሩን መመሪያ ማሻሻልና በአንድ ወጥ አዲስ መመሪያ መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር በደንብ ቁጥር 88/95 አንቀጽ 3 እና በደንብ ቁጥር 6/88 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ለ(2) ለ መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ በልዩ መብት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ የግል መገልገያ እቃዎች፣ ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 7/1996 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**አንቀጽ 2 ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር:-

1) «ስደተኛ» ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ከአገሩ ወጥቶ በስደት የኖረና በራሱ ፈቃድ ወይም በመንግሥት ስምምነት ያለፓስፖርት ወደአገሩ የሚመለስ ወይም በተቀባይ አገር የጥገኝነት ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘ እና በራሱ ፈቃድ በሊሴ ፖሴ ወይም በነበረበት አገር መንግስት ተገዶ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ነው::

2) «ተመላሽ» ማለት በሕጋዊ መንገድ ከኢትዮጵያ ወጥቶ በሄደበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ አግኝቶ የኖረና ጠቅልሎ የሚመለስ ወይም ሕጋዊ ወይም ሕጋዊ ባልሆኑ የተለያዩ መንገዶች ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ ከኢትዮጵያ ኤምባሲ የአገሩን ፓስፖርት እንደዚሁም ከኖረበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ አግኝቶ የኖረና ጠቅልሎ የሚመለስ ነው:: የመኖሪያ ፈቃድ አሰራር በሌለበት አገር የኢትዮጵያን ፖስፖርት የያዙና እያሳደሱ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በዚህ ትርጉም የሚሸፈኑ ይሆናሉ::

3) «ትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋ» ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጐችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 270/94 መሠረት በወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት የኢትዮጵያ ተወላጅ የውጭ ዜጋ የመታወቂያ ካርድ የተሰጠው ሰው ሲሆን የመታወቂያ ካርዱ ጊዜውን ጠብቆ የታደሰለት እና ያልተሰረዘበት ነው::

4) «ዲፕሎማት» ማለት በኢትዮጵያ ሚሲዮን ወይም ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ በዲፕሎማትነት የተመደበ ወይም በኋለኞቹ ተቋማት ውስጥ ራሱ ተወዳድሮ የተቀጠረና የዲፕሎማቲክ ማዕረግ

